# የቸኮለ...



14-17ኛው ሳምንት

2ኛ ክፍል

መጽሐፍ 10

# የቸኮለ...

መጽሐፍ 10 | 2ኛ ክፍል | 14-17ኛው ሳምንት



ይህ አጋዥ የንባብ መጽሐፍ ከዩ.ኤስ.ኤ.አይ.ዲ. (USAID) በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ በፓክት ኢትዮጵያ (Pact Ethiopia) እና በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ የጋራ ትብብር ተዘጋጅቶ በሴቭ ዘ ቺልድረን (Save the Children) እና በትምህርት ሚኒስቴር ተሻሽሎ ታተመ።

The CC By license lets others distribute, adjust, and build upon this work, for free or commercially, as long as credit is given to the original creation. However, any changes from the original must be indicated.
For more info please refer: *https://creativecommons.org/licenses/*



የምግብ ጠረጴዛው በተለያዩ ምግቦች ተሞልቷል።

ከበሽታ ተከላካይ ሰላጣ፣ ቆስጣ፣ የአበሻ ጎመን ይታያሉ። ከገንቢ ምግቦች የክክ ወጥ፣ የስጋ ወጥ፣ የእንቁላል ጥብስና የአሳ ዱለት ቀርበዋል።

ከሀይልና ሙቀት ሰጪ
ምግቦች ደግሞ የድንች
ጥብስና ዳቦ ተደርድረዋል።



ልጁ ገና ምግቡን ሲያየው
የምግብ አምሮቱ ተቀሰቀሰ::
በመቻኮል ከየምግብ ዓይነቱ
የቻለውን ያህል አነሳና
ተቀመጠ:: የሚጠጣው ውሃ
ግን አላቀረበም:: ቶሎ ቶሎ
ጎረሰ::



ምግቡን ሳያላምጥ ለመዋጥ
ሲሞክር ከጉሮሮው አልወርድ
አለው:: ዓይኖቹ ፈጠጡ::
ላብ አጠመቀው:: እናቱን
ሊጣራ ፈለገ:: አልቻለም::
ጉሮሮውን እንደያዘ ወደእናቱ
ሮጠ::

እናቱ ልጄ ምን ሆነ
ብለው ደነገጡ። ውሃ
እንደሚፈልግ በምልክት
አሳያቸው።



ውሃ በፍጥነት አንስተው ሰጡት:: ውሃውን እንደጠጣ በረጅሙ ተነፈሰ::

እናቱም “ልጄ ስትመገብ
በቅድሚያ መጥኖ መጉረስ
ያስፈልጋል፡፡ የጎረሱትን
በደንብ አላምጦ መዋጥ
የግድ ነው፡፡ ምግብ በትክክል
ካልተላመጠ ወደአየር ቧንቧ
ይሄድና ትንፋሽ አሳጥቶ
ለሞት ያደርሳል” አሉት፡፡

USAID

ከአሜሪካን ሕዝብ